# 480

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በአርበኞች ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ የተቋቋመውን ፡ አዲሱን ፡ የኦቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያና ፡ በፍል ፡ ውሃ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ የተሠራውን ፡ አዲሱን ፡ ያገር ፡ ውስጥ ፡ የቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ መጋቢት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፲ ፡ ሰዓት ፡ መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

ሀ) የፖስታ ፡ ቴ . ቴ ፡ ሚኒስትር ፡ የክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ዛሬ ፡ እነዚህን ፡ በመጨረሻው ፡ ቴክኒክ ፡ ጥበብ ፡ የተሠሩትን ፡ የአዲስ ፡ አበባን ፡ የቴሌፎን ፡ ኦቶማቲክ ፡ ማዞሪያዎችና ፡ መናገሻውን ፡ ከተማ ፡ ከየጠቅላይ ፡ ግዛቶችና ፡ ከአውራጃዎች ፡ ጋር ፡ የሚያገናኘውን ፡ አዲስ ፡ ማዞሪያ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ ሊመርቅልን ፡ በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ ስለተገኘልን ፡ በፖስታ ፡ ቴሌግራፍና ፡ ቴሌፎን ፡ ሚኒስትርነቴና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ጥልቅ ፡ የሆኑ ፡ ምስጋናዎቼን ፡ እጅግ ፡ ከተከበረው ፡ ዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቁሜ ፡ አቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይፍቀድልኝ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ ባገራችን ፡ የተቋቋመው ፡ ከዛሬ ፡ ፶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ግርማዊነትዎም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መሪነት ፡ እንደተመረጡ ፡ ጀምሮ ፡ ላገሪቱ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ልማት ፡ ለሕዝቡ ፡ አገልግሎት ፡ ለመንግሥቱም ፡ ያስተዳደር ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊዎች ፡ ሆነው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ካቀዳቸው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ እንዲሆን ፡ ስለወሰነ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሁኔታውን ፡ በትጋት ፡ በመከታተል ፡ በየጊዜው ፡ በሰጣቸው ፡ የሥራ ፡ መሪ ፡ ትእዛዞች ፡ መሠረት ፡ የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ በከተማዎችና ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ጭምር ፡ ከዓመት ፡ ዓመት ፡ ይበልጥ ፡ እየተስፋፋና ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄድዋል ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ የሚፈጸመው ፡ የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ አሁን ፡ አገራችን ፡ ለምታደርገው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርዳታ ፡ ያደረገ ፡ መሆኑን ፡ ሳስብ ፡ የሚሰማኝ ፡ ደስታ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የምንገኝበት ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የችኮላና ፡ የእሽቅድድም ፡ ስለሆነና ፡ የሁሉም ፡ መቃረብ ፡ ስላስፈለገ ፤ አገራችንም ፡ በዚሁ ፡



መጠን ፡ በቅልጥፍና ፡ እንድትራመድ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ያሰበበት ፡ ስለሆነ ፤ የዛሬ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ እንዲቋቋም ፡ ፈቀደ ።

ቦርዱም ፡ ለመሣሪያዎች ፡ መግዣ ፡ የተፈቀደለትን ፡ የዓለም ፡ ባንክ ፡ ብድር ፡ የተቀበለው ፡ ሥራውን ፡ ከተረከበ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ስለሆነ ፤ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ በአዲስ ፡ ዐቅድ ፡ ለማቋቋም ፡ ከማደራጀትና ፡ የነበሩትን ፡ የቴሌፎንና ፡ ቴሌግራፍ ፡ መሣሪያዎችና ፡ ንብረቶች ፡ ከመረከብ ፡ ከማደስና ፡ ከመለወጥ ፡ በቀር ፡ አዲስ ፡ መሣሪያዎች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ለማስመጣት ፡ አልቻለም ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ መጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ የቴሌፎኑና ፡ የቴሌግራፉ ፡ አገልግሎት ፡ የሚገኝበትን ፡ ሁኔታ ፡ ለማጥናትና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሊገዙ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ዝርዝርና ፡ ዋጋቸውን ፡ በማጥናት ፡ ለማወቅ ፡ ችሎ ፡ ቆየ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ባለፈው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የዓለም ፡ ባንክ ፡ ሊያበድር ፡ የፈቀደውን ፡ ገንዘብ ፡ ቦርዱ ፡ ለመቀበል ፡ እንዲችል፡ ስለሆነለት ፡ ሥራውን ፡ በሰፊው ፡ ጀመረ ። በዚሁ ፡ መጨረሻ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከፈጸማቸው ፡ ታላላቅና ፡ አዳዲስ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ የነዚህ ፡ የቴሌፎን ፡ ኦቶማቲክ ፡ ማዞሪያዎች ፡ መቋቋም ፡ ሆኖ ፡ ዛሬ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ለመመረቅ ፡ በመድረሱ ፡ ለቦርዱ ፡ የሚሰማው ፡ ደስታ ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ አሁን ፡ የሚመረቁት ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ማዞሪያዎች ፡ ከዚህ፡ ቀደም ፡ ከነበረው ፡ ኦቶማቲክ ፡ ማዞሪያ ፡ ከሦስት ፡ እጅ ፡ ለበለጠ ፡ የቴሌፎን ፡ ደንበኞች ፡ ሊያገለግሉ ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ። መናገሻውን ፡ ከተማ ፡ ከጠቅላይ ፡ ግዛቶችና ፡ ከአውራጃዎች ፡ ጋር ፡ የሚያገናኘውም ፡ ማዞሪያ ፡ ለዚሁ ፡ አገልግሎት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከነበረው ፡ ማዞሪያ ፡ ከ፩ ፡ እጅ ፡ የሚበልጥ ፡ ድርጅት ፡ የሚገኝበት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የነዚህ ፡ ማዞሪያዎች ፡ ችሎታ ፡ አሁን ፡ ካላቸው ፡ በላይ ፡ እንዲሆን ፡ በሚያስፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለመጨመር ፡ ሲታሰብ ፡ በቀላል ፡ መንገድ ፡ ለመጨመር ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ የአሠራራቸው ፡ አኳኋን ፡ የሚፈቅድ ፡ ነው ።

ጃንሆይ ።

ንግግሬን ፡ ከመጨረሴ ፡ በፊት ፡ የቦርዱን ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ፡ ሚስተር ፡ ኖርበርግን ፡ በሥራቸው ፡ ሳላመሰግናቸው ፡ ማለፍ ፡ አይገባ ኝም ። ለወደፊቱም ፡ በብዙ ፡ ትጋት ፡ ሥራቸውን ፡ እንደሚቀጥሉ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። እንዲሁም ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የተቀጠ ሩት ፡ ቴክኒሲያኖችና ፡ የአገራችንም ፡ ልጆች ፡ በትጋት ፡ በመሥራታ ቸው ፡ አመሰግናቸዋለሁ ።

የታወቀውም ፡ የኤሪክስን ፡ ፋብሪካ ፡ ዋና ፡ ዲሬክተርና ፡ ሹማምን ቶች ፡ ለነዚህ ፡ የቴሌፎን ፡ አቶማቲክ ፡ ማዞሪያዎች ፡ መቋቋም ፡ በመግ ባባት ፡ መንፈስ ፡ ላደረጉልን ፡ እርዳታ ፡ አመሰግናቸዋለሁ ።

የቦርዱም ፡ አባሎች ፡ በሌላ ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፡ ደርሰው ፡ ለቴሌኮ ሙኒኬሽኑ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በታላቅ ፡ ትጋት ፡ በሚሰጡት ፡ ዲሬክቲ ፍና ፡ እርዳታ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ስላሰኙ ፡ ምስጋናዬ ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ የቦርዱ ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በበኩላቸው ፡ የሥራውን ፡ ዝርዝር ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ እንዲገልጹ ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ እለምናለሁ ።

ጥሪያችንን ፡ ተቀብለው ፡ ለመጡልን ፡ ልዑላን ፡ መሳፍንት ፤ ሚኒ ስትሮችና ፡ መኳንንቶች ፤ የውጭ ፡ አገር ፡ እንደራሴዎችና ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ምስጋናዬን ፡ በቦርዱና ፡ በራሴ ፡ ስም ፡ አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፤
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ በነፃነት ፡ ትኑር ።

✻ ✻ ✻

ለ) የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የሚስተር ፡ ኖርበርግ ፡ ንግግር ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ እ ፡ አ ፡ አ ፡ ቊጥር ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ።

ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የቴሌፎን ፡ መስመሮች ፡ እንዲጠ



ረጉ ፡ ለጊዜው ፡ አስፈላጊና ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሥራ ፡ እንዲቀ ድም ፡ ሆኖ ፡ የቴሌፎን ፡ ማዞሪያዎችን ፡ ፈታትቶ ፡ ገጠመ ።

ስልከኞችንና ፡ የመሥመር ፡ ሠራተኞችን ፡ ማሠልጠን ፡ ጀመረ ። ከ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ. ም. እስከ ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ. ም. እስከ ፡ ጥር ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ የቴ ሌፎን ፡ ትራፊክ ፡ መጠን ፡ እያደገ ፡ በመሄዱ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ አስቸ ጋሪ ፡ ሁኔታዎችን ፡ አስከትሎ ፡ ነበር ።

በኦቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ላይ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ተጭኖት ፡ የነበረ ውን ፡ የመሥመሮች ፡ ብዛት ፡ ለማቃለልና ፡ አዲስ ፡ የቴሌፎን ፡ ማኅበረ ተኛን ፡ ለመቀበል ፡ ለጊዜው ፡ የሚያገለግል ፡ አንድ ፡ የማኅበሩ ፤ በእጅ ፡ በማዞር ፡ የሚደውል ፡ የቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ክፍል ፡ ውሃ ፡ ተቋቋመ ።

ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ሕዝቡ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ያለማቋረጥ፡ ይጠይቅ ፡ ነበር ። ፍል ፡ ውሃ ፡ ላይ ፡ በቆመው ፡ የማንዋል ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞ ሪያ ፡ ፋንታ ፡ ለምን ፡ የኦቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ አይቆምም ? አዲ ሱን ፡ የኦቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ለማቆም ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ይፈጃል ? እዚህ ፡ ላይ ፡ ምክንያቱን ፡ ማስረዳት ፡ አስፈላጊ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ የኦቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ከመገዛቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ መሥመሮቹ ፡ መገናኛዎች ፡ ድርጅት ፡ ለማዞሪያው ፡ መኪና ፡ በቴ ክኒክ ፡ ረገድ ፡ ስለሚያስፈልጉዋቸው ፡ ጉዳዮች ፡ እንደ ፡ ትራፊክ ፡ ለመ ሳሰሉትም ፡ ሌሎች ፡ ነገሮች ፡ በታላቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ፕላን ፡ ማዘጋጀት ፡ አለበት ። ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ጨረታዎች ፡ ተጠይቀው ፤ የሚቀርቡት ፡ የዋጋ ፡ ጨረታዎች ፡ መመርመር ፡ አለባቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መሣሪያ ዎቹ ፡ በግዥ ፡ ከውጪ ፡ አገር ፡ የታዘዙት ፡ በፋብሪካም ፡ ተሠርተው ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ተልከው ፡ ተቋቊመው ፡ ይፈተሻሉ ፡ ይሞከራሉ ።

ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ በግዥ ፡ ለሚታዘዙት ፡ መሣሪያዎች ፡ እስከ ፡ ተወሰነ ፡ መጠን ፡ ድረስ ፡ ዋጋቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ይከፈላል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነው ። እውነቱን ፡ በመናገር ፡ ቦርዱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ጉዳዮች ፡ ለማከናወን ፡ የሚያስፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ እስከ ፡ የካቲት ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ( ማለት ፡ የዛሬ ፡ ዓመት ፡) ይህ ፡ አል ደረሰውም ፡ ነበር ። ጨረታዎቹ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ተመርምረው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ገንዘቡ ፡ ዝግጁ ፡ እንደሆነ ፤ ወዲያውኑ ፡ መሣሪያዎቹ ፡ ከውጭ ፡

አገር ፡ ታዘዙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአዲስ ፡ ኬብል ፡ መሥመር ፡ መገናኛዎች ፡ ድርጅት ፡ መቋቋም ፡ ሥራ ፡ ባለፈው ፡ ግንቦት ፡ ወር ፡ ሲጀመር ፡ ቀጥሎም ፡ የአዲሱ ፡ አቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ማቋቋም ፡ ሥራ ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ተጀመረ ። ዛሬ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ሁናቴን ፡ ስንመለከተው ፤ እነዚህ ፡ መሣሪያዎች ፡ በፍጥነት ፡ ደረሱልን ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። ደንበኞቻችን ፡ መልካም ፡ የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ ለማግኘት ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ፈጅብን ፡ ብለው ፡ ወቀሳ ፡ ያቀረቡ ፡ እንደሆነ ፡ ክቡራን ፡ ደንበኞች ፡ ቦርዱ ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ የተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ነበር ፤ ይልቁንም ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያው ፡ ማቋቋም ፡ ሥራ ፡ ገንዘቡ ፡ ወጪ ፡ በሆነ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ሆነለትና ፡ ታማኝ ፡ በሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ ብርታት ፡ በሙሉ ፡ በመከናወኑ ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ፡ ብለን ፡ መልስ ፡ ልንሰጣቸው ፡ ይገባናል ።

የአንድ ፡ አቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ማቋቋምና ፡ መፈተን ፡ በሰፊው ፡ የቴክኒክ ፡ ችሎታንና ፡ ልምድን ፡ የሚጠይቅ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በዚህ ፡ በአዲሱ ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ሊፈተኑና ፡ በትክክል ፡ መሥራት ፡ ያለባቸው ፡ 2 . 400. 000. የኮንታክት ፡ ሥፍራዎች ፡ አሉ ። እንዲሁም ፡ በርሳስና ፡ በሌሎች ፡ ማጣበቂያዎች ፡ የተገጠሙ ፡ 750 . 000. ሥፍራዎች ፡ ሲገኙበት ፡ የማዞሪያውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ የሚያገናኙ ፡ ረቂቅ ፡ ሽቦዎች ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ፹፯ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጠን ፡ ያሉዋቸው ፡ አዳዲስ ፡ ኬብልስ ፡ (ካቦ) ፡ የዘረጋን ፡ ስንሆን ፡ በነዚህ ፡ ኬብልስ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሽቦዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ርዝመት ፡ ፫ሺ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ይሆናል ። ለአዲሱ ፡ አቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ አዲስ ፡ የቴሌፎን ፡ መገናኛዎች ፡ ድርጅት ፡ በጠቅላላው ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ተኩል ፡ (1.500.000 የኢት ፡ ብር ፡ ያህል ፡ ወጪ ፡ ሆኖአል ። በንግግሬ ፡ ውስጥ ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ እንዳመለከትሁት ፡ አሮጌው ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ችሎታ ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ 1500 ፡ መሥመሮች ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ አዲሱ ፡ አቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ግን ፡ በመጀመሪያው ፡ እስከ ፡ 4600 ፡ መሥመሮች ፡ በማገልገልና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ መጠን ፡ መሥመ-



ሮች ፡ እየጨመረ ፡ በመሄድ ፡ አኳኋን ፡ ለማስፋፋት ፡ እንዲመች ፡ ታቅዶ ፡ የተሠራ ፡ ነው ።

የአሮጌው ፡ አቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ትራፊክ ፡ ችሎታ ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ሁሉ ፡ በፍጥነት ፡ እያደገ ፡ ለሚሄደው ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ከአሁን ፡ በፊት ፡ እንዳወጣነው ፡ የትራፊክ ፡ ስታቲስቲክ ፡ ዝርዝር ፡ የቴሌፎን ፡ ጥሪዎች ፡ በሚበዙባቸው ፡ ሰዓቶች ፡ ውስጥ ፡ የያንዳንዱ ፡ ሁለተኛ ፡ ጥሪ ፡ ሳይተላለፍ ፡ እንደሚቀር ፡ ተረጋግጧል ። የአዲሱ ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ ችሎታ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፤ አንድ ፡ የቴሌፎን ፡ ማኅበረተኛ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ጥሪው ፡ ሳይተላለፍ ፡ ቢቀር ፡ ነው ። አሮጌው ፡ የቴሌፎን ፡ መገናኛዎች ፡ ድርጅት ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ አንድ ፡ መሰናክል ፡ ይገጥመው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በአዲሱ ፡ የቴሌፎን ፡ መገናኛዎች ፡ ድርጅት ፡ ግን ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ መሰናክል ፡ ቢገጥመው ፡ ነው ። የአዲሱ ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ትራፊክ ፡ በቀላሉ ፡ ለመጨመር ፡ በሚያስችል ፡ አኳኋን ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፤ ከጥቂት ፡ ወሮች ፡ በኋላ ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ መገናኛ ፡ ትራፊክ ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በቢሸፍቱ ፡ መካከል ፡ ሲቋቋም ፤ ከዚያም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ከአንድ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ይቀጥላል ።

አዲስ ፡ የአቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያ ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ ከተያዘ ፡ እስከ ፡ ፵ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ይበልጥ ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ ለመሥራት ፡ ይችላል ። አሁን ፡ ስለ ፡ ቴሌፎን ፡ ኪራዮች ፡ ዋጋ ፡ ጥቂት ፡ መልካም ፡ ቃሎች ፡ ጨምሬ ፡ ለማስረዳት ፡ ደስ ፡ ይለኛል ። የዛሬ ፡ ዓመት ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ የያንዳንዱ ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ ቴሌፎን ፡ ኪራይ ፡ በወር ፡ ፱ ፡ የኢት. ብር ፡ ነበር ። ደግሞ ፡ የግል ፡ (የቤት) ቴሌፎን ፡ ኪራይ ፡ ፰ ፡ የኢት. ብርና ፡ ደግሞ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ወጪ ፡ ጥሪ ፡ ፲ ፡ የብር ፡ ሳንቲም ፡ ይጠየቅበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ቦርዱ ፡ እነዚህን ፡ አዳዲስ ፡ ማዞሪያዎች ፡ በማቋቋሙ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የቴሌፎን ፡ ማኅበረተኞች ፡ (ተከራዮች) ፡ ሁሉ ፡ ከመጋቢት ፡ ፩ ፡ ጀምሮ ፡ ለግል ፡ ቴሌፎናቸው ፡ ኪራይ ፡ በወር ፡ ፰ ፡ የኢት ፡ ብርና ፡ ለያንዳንዱ ፡ ወጪ ፡ ጥሪ ፡ ፯ ፡ የብር ፡ ሳንቲም ፡ እንዲከፍሉ ፡ በመወሰኑ ፡ ኪራዩን ፡ ለማስተካከል ፡ ችለ-

ዋል ። ስለዚህ ፡ ለወደፊቱ ፡ በአዲሱ ፡ የኪራይ ፡ ዋጋ ፡ ዝርዝር ፡ የቴሌፎን ፡ ማኅበረተኛ ፡ (ተከራይ) ለመሆን ፡ የሚጠይቁትን ፡ ሰዎች ፡ በደስታ ፡ መቀበሌን ፡ እየገለጽሁ ፡ ቦርዱ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በቴሌፎን ፡ መጠቀም ፡ እንዲቀነስ ፡ በማለት ፡ ፋንታ ፡ የቴሌፎን ፡ አገልግሎት ፡ በተቻለ ፡ መጠን፡ በሰፊው ፡ እንዲሠራበት ፡ ለማደፋፈር ፡ ችሎዋል ፡ ስል ፡ ይህን ፡ ለመፈጸም ፡ ላስቻለን ፡ ፈጣሪ ፡ ምስጋና ፡ በማቅረብ ፡ ነው ። ይህ ፡ አዲስ ፡ የቴሌፎን ፡ መገናኛዎች ፡ መሥመር ፡ በመናገሻው ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሲዘረጋ ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤትና ፡ ከሸዋ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ጋር ፡ ተባብሮ ፡ በመሥራቱ ፡ ይህንኑ ፡ የዛሬውን ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለነዚህ ፡ ለሁለት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ምስጋናዬን ፡ ላቀርብ ፡ እወዳለሁ ።

እንዲሁም ፡ እነዚህ ፡ ማዞሪያዎች ፡ በተቋቋሙበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሥራው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመተባበር ፡ ተግባር ፡ ላሳዩት ፡ ለኤሪክስን ፡ ኩባንያ ፡ ሠራተኞች ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ። እንዲሁም ፡ በመጨረሻ ፡ በቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ድርጅት ፡ በእኔ ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ሹማምንቶችና ፡ ሠራተኞች ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ዓመታትና ፡ ይልቁንም ፡ በመጨረሻዎቹ ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ ላሳዩት ፡ የመተባበር ፡ ሥራና ፡ መልካም ፡ የብርታት ፡ መንፈስ ፡ በብዙ ፡ አመሰግናቸዋለሁ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጕዳናዎች ፡ አዲሱን ፡ ታሪካዊ ፡ ዘመን ፡ ከፍተዋል ። እንዲሁም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እነዚህን፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የተቋቋሙትን ፡ አዲስ ፡ ማዞሪያዎች ፡ በመመረቅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለቴሌኮሙኒኬሽን ፡ መገናኛዎችም ፡ አዲስ ፡ ታሪካዊ ፡ ዘመን ፡ እንዲከፍቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ልመናዬን ፡ በትሕትና ፡ ለግርማዊነትዎ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ የአዲሶቹ ፡ ኦቶማቲክ ፡ ቴሌፎን ፡ ማዞሪያዎች ፡ መከፈት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ ላቀድነው ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ እድገትና ፡ መስፋፋት ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ እርምጃ ፡ ነው ።



በመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ በዘመኑ ፡ ጥበብ ፡ ተሠርቶ ፡ የተቋቋመው ፡ የስልክ ፡ ድርጅት ፡ በጠቅላላው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችንና ፡ እንደዚሁም ፡ ከውጭው ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ ሊኖረን ፡ የሚገባውን ፡ ግንኙነት ፡ ለማስፋፋት ፡ እስካሁን ፡ ለተሠራው ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ ለታቀደው ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ መሠረት ፡ ሆኖዋል ።

የሁለቱ ፡ ኦቶማቲክ ፡ ማዞሪያዎች ፡ መቋቋም ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመቶች ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የመገናኛ ፡ ችግር ያስወግዳል ፡ ብለን ፡ ተስፋ፡ እናደርጋለን ። ችግሩ ፡ ሊወገድ ፡ የሚችለው ፡ ማዞሪያዎቹና ፡ መገናኛ ፡ ሽቦዎቹ ፡ በደኅና ፡ ሲጠበቁና ፡ የተበላሸም ፡ ነገር ፡ ሲገኝ ፡ ወዲያው ፡ በፍጥነት ፡ እንዲጠገን ፡ በማድረግ ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

የዚሁኑ ፡ ያህል ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሊሰጠውና ፡ ሊታሰብበት ፡ የሚገባው፡ ተከታዩ ፡ ጉዳይ ፡ ለቴክኒክና ፡ ለአድሚኒስትሬሽን ፡ ሥራ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወጣቶች ፡ ማሠልጠን ፡ ስለሆነ ፤ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ የሆኑት ፡ የኢንተርኔሽናል ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ዩንየን ፡ ዐዋቂዎች ፡ በሚያደርጉት ፡ ሰፊ ፡ የትምህርት ፡ እርዳታ ፡ ልናመሰግናቸው ፡ እንወዳለን ።

የቦርዱ ፡ ፕሬዚዴንትና ፡ አባሎች ፤ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ድርጅት ፡ ጠቅላይ ፡ መሪ ፡ የሆኑትና ፡ የቀሩትም ፡ ሠራተኞች ፡ የነዚህን ፡ ኦቶማቲክ፡ ማዞሪያዎች ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ባደረጉት ፡ ጥረትና ፡ ትጋት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

እንደዚሁም ፡ የታወቀው ፡ የኤሪክስን ፡ ስልክ ፡ ካምፓኒ ፡ ዋና ፡ ዲሬክተርና ፡ ሠራተኞች ፡ ለዚህ ፡ ድርጅት ፡ ላደረጉት ፡ እርዳታና ፡ ላሳዩት ፡ ኅብረት ፡ እያመሰገንን ፡ እነዚህን ፡ ኦቶማቲክ ፡ ማዞሪያዎች ፡ እንከፍታለን ።

# 481

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መጋቢት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከእኩሉ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በራት ፡ ጊዜ ፡ በተማሪዎቹ ፡ የምግብ ፡ ቤት ፡ ተገኝተው ፡ ተማሪዎቹን ፡ ሲጐበኙ ፡ የተነገሩት ፡ ቃሎች ።

ሀ) ከተማሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ ተሾመ ፡ ተሰማ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ ለማድረስ ፡ ከሚጥረው ፡ ከብዙዎቹ ፡ መልካም ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሥጋዊ ፡ ትምህርት፡ ብቻ ፡ ለሀገር ፡ ሥልጣኔን ፡ የማይሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝበ ፤ ይህን ፡ የቅድስት ፡ ሥላሴን ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማቋቋሙ ፡ ለሁሉም ፡ ትውልድ ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለም ፤ ይልቁንም ፡ ይህ ፡ ያለው ፡ ትምህርት ፡ ቤት፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ በቂውን ፡ ትምህርት ፡ ሊሰጥበት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ ኮሌጅ ፡ እንዲሠራ ፡ በማድረግዎ ፡ ከነዚህ ፡ ከሚመለከቷቸው ፡ ወጣቶች ፡ መካከል ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ዕድሜ ፡ ፈጣሪውን ፡ የማይለምን ፡ በፍጹም ፡ አይገኝም ። ከዚህ ፡ አሁን ፡ ካለንበት ፡ የበለጠ ፡ ይሰጡን ፡ ዘንድ ፡ ለጊዜው ፡ የምንለምንዎ ፡ ስለሌለን ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክን ፡ የምንለምነው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለደጉ ፡ ንጉሣችን ፡ ረጅሙን ፡ ዕድሜ ፡ ይሰጥልን ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

* * *

ለ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

እኛም ፡ በነገሩ ፡ በሰፊው ፡ አስበንበታልና ፡ በርትታችሁ ፡ ተማሩ ፤ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ የለም ።

---

# 482

የሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ኤል ፡ ሳይድ ፡ እስማኤል ፡ ኤልአዝሃሪ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በተደረገላቸው ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ከሚያዝያ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ለአምስት ፡ ቀኖች ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፡ ሚያዝያ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኀሙስ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ለመመለስ ፡ በተነሡበት ፡ ጊዜያት ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ። እንዲሁም ፡ የሱዳን ፡ ራዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በተደረገላቸው ፡ ኦፊሴላዊ ፡ አቀባበል ፡ የሱዳን ፡ ሕዝብ ፡ መደሰቱን ፡ በመግለጽ ፡ ሚያዝያ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከማታው ፡ በ፪ ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የደስታ፡ መግለጫ ፡ ቃል ፡ አስተላለፈ ። ንግግሮቹ ፡ ሁሉ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።



ሀ) የሱዳን ፡ ራዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ ያስተላለፈው ፡ ቃል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ የሱዳን ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ኤል ፡ ሳይድ ፡ እስማኤል ፡ ኤልአዝሃሪ ፡ ከሱዳን ፡ ሚኒስትሮች ፡ ጋር ፡ ጎረቤትና ፡ ወዳጃችን ፡ የሆነችውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመጐብኘት ፡ በተደረገው ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፡ በተባለው ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ በዋናው ፡ መናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ለክቡር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትራችንና ፡ ለሚኒስትሮቻችን ፡ በተደረገላቸው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝና ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ አቀባበል ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜና ፡ መልካም ፡ ምኞታችንን ፡ እና ቀርባለን ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ሱዳንና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ጥቅም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የተሳሰረ ፡ ቢሆንም ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መገናኛ ፡ ኪዳናዊ ፡ የሆነው ፡ የዓባይ ፡ ውሃ ፡ በቂ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ ችሎአል ።

ስለዚህና ፡ ስለማናቸውም ፡ የኢትዮጵያና ፡ የሱዳን ፡ ሕዝብ ፡ ፍቅር ፡ የሚዘነጋ ፡ ስላልሆነ ፡ ገናና ፡ ለሆነው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜና ፡ ለተወደደውም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምና ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ እንመኛለን ።

* * *

ለ) የጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የክቡር ፡ ኤል ፡ ሳይድ ፡ እስማኤል ፡ ኤልአዝሃሪ ፡ ንግግር ።

ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በተደረገልኝ ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመጐብኘት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ ለተደረገልን ፡ ከፍተኛ ፡ አቀባበል፡ ከልባችን ፡ እናመሰግናለን ። በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል፡ ያለው ፡ ወዳጅነት ፡ በሚያስደስት ፡ አኳኋን ፡ እየጠነከረ ፡ እንደሚሄድ ፡ እርግጠኞች ፡ ነን ።

ይህችን ፡ ብልጽግና ፡ የተሞላባትን ፡ አገር ፡ የማይመለከት ፡ የለም ፤ ታላቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሁለተኛው ፡ ጉዞ ፡ ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ሲሄዱና ፤ ወደ ፡ ተወደደችው ፡ አገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ በሱዳን ፡ በኩል ፡ ስለሆነ ፤

በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ብዙና ፡ ጠቃሚ ፡ ነገሮችን ፡ ለመነጋገር ፡ አስችሎናል ።

እንዲሁም ፡ ይህችን ፡ ብልጽግና ፡ የተሞላባትን ፡ አገር ፡ እግራችን ፡ ሊረግጣት ፡ በመቻሉ ፡ የተሰማን ፡ ደስታ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ተገኝ ቶአል ።

ታላቁ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ልባቸውን ፡ ከፍተው ፡ ተቀብ ለው ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ እንደሚነጋገረው ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ እንደ ፡ ልጆቻቸው ፡ በምክር ፡ አነጋገሩን ። እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ ስናነጋግር ፡ በግልጽ ፡ አንደበትና ፡ የልባችንን ፡ ሁሉ ፡ ያለችግር ፡ ለመናገር ፡ በመቻላችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ አግኝተናል ።

ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ያገኘነው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው፡ አቀባበል ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ርኅሩኅነትን ፡ የተሞላ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፤ በመልካም ፡ ዝግጅት ፡ የተደራጀ ፡ ነው ።

በጠቅላላው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለተደረገልን ፡ አቀባበል፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርባለን ። ደግሞም ፡ ታላቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ያደረጉልንን ፡ ታላቅ ፡ ሽልማት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ኩራትና ፡ በሙሉ ፡ ልባችን ፡ ደረታችን ፡ ላይ ፡ ስናደርገው ፡ የተሰ ማን ፡ ደስታና ፡ ኩራት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመግለጽ ፡ አስቸ ጋሪ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ለደም ፡ ሥራችን ፡ ማንቀሳቀሻ ፡ ሊሆነን ፡ ችሎ አል ።

እኔና ፡ ወንድሞቼ ፡ ይህን ፡ የተወደደውን ፡ ዋና ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ስንተው ፡ በጣም ፡ ቅር ፡ እያለን ፡ ነው ።

ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴና ፤ ለግርማ ዊት ፡ እቴጌ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ እንመኛለን ። እንዲሁም ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ላደረጉልን ፡ ታላቅ ፡ አቀባበል ፡ እናመሰግ ናለን ።

ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ለወዳጅና ፡ ለሌሎ ቹም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ላደረጉልን ፡ አቀባበል ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናቸ ዋለን ።

ጎረቤትና ፡ ወዳጅ ፡ የሆነችው ፡ አገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ሆና ፡ ብልጽግናና ፡ ከፍተኛነት ፡ እንደ ፡ ያዘች ፡ ለዘላ



ለም ፡ እንድትኖር ፡ ምኞታችንን ፡ እንገልጻለን ።

---

# 483

፲፩ኛው ፡ ዓመት ፡ የነፃነት ፡ በዓል ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ.ም. በ፯ ፡ ሰዓት ፡ በታ ላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲከበር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳል ካቸው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ሀ) የክቡር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ በመከራ ፡ ተፈትነን ፡ አገራችን ፡ ተመልሰን ፡ ከገባን ፡ ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ሆነ ።

በዚህች ፡ በጥቂት ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ መከሩ ፡ ብዙ ፡ ሆኖ ፡ ሠራተኛው ፡ ጥቂት ፡ ቢሆን ፤ ግርማዊነትዎ ፡ ወርቅ ፡ የሆነ ፡ ጊዜዎን ፡ ሳያ ጠፉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልማትና ፡ ስፋት ፡ የሠሩዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። በዝርዝር ፡ ለመናገር ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

አንድ ፡ አገር ፡ ከትልልቅ ፡ መንግሥታት ፡ ተራ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የሚቈጠረው ፡ ባገሩ ፡ ስፋትና ፡ በሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ አይደለም ። አገርን ፡ ከፍ ፡ የሚያደርገው ፡ በመንፈስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመንግሥት ፡ መሪ ፡ ከእግዚ አብሔር ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ለዚህ ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ ተግባር ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተመር ጠው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሲሰጡ ፤ ስለ ፡ ሀገርዎ ፡ ያደረጉት ፡ መልካም ፡ አመራ ርና ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ሥራዎች ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ የታቀዱትን ፡ ሰፊ ፡ ፕሮግራሞች፡ ከግባቸው ፡ ለማድረስ ፡ ዋና ፡ የሚያስፈልገው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ዕድሜና፡ ጤና ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ በራሴም ፡ ስም ፡ ሆኜ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ረጅም ፡ ዘመንና ፡ ጤና ፡ ሰጥቶ ፡ በያመቱ፡ ከዙፋንዎ ፡ ላይ ፡ እንድናይዎ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምናለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

በሰው ፡ ምኞትና ፡ ሥልጣን ፡ ሊገለጥ ፡ የማይቻለውን ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ ስላደረገልን ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ለእርሱ ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ እያልን ፡ እንግዲህ ፡ ውለታውን ፡ የምንመልስለት ፡ ለእኛ ፡ ሊያደርግልን ፡ የምንወደውን ፡ በእኛም ፡ በኩል ፡ ለሕዝባችን ፡ እንዲደርሰው ፡ በማድረግና ፡ በመረዳዳት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ለሕዝባችን ፡ እንዲደርሰው ፡ ካልነው ፡ ከብዙዎቹ ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፤ አእምሮው ፡ የሚጐለምስበትን ፤ ጤናው ፡ የሚጠበቅበትን ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምነት ፡ የሚመራበትን ፡ እንድንሠራለት ፡ እርዱን ፤ ተከተሉን ።

በዚያ ፡ በመከራው ፡ ሰዓት ፡ ከውጭም ፡ ሆነ ፡ ከግቢ ፤ ያላዘነ ፡ አይገኝም ። ይልቁንም ፡ አርበኞች ፡ በጽኑዕ ፡ ተጋድሎና ፡ መከራ ፡ የተፈተኑበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ሰው ፡ ሊያፈርሰው ፡ የማይችለውን ፡ በቸርነቱ ፡ ከባዱን ፡ አቀለለልን። የሰው ፡ ሥራ ፡ ፈራሽ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ነዋሪ ፡ ለመሆኑ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ባደረገው ፡ ቸርነት ፡ እንረዳዋለን ።

ለእኛ ፡ ሊያደርግልን ፡ በምንወደው ፡ አኳኋን ፡ ውለታውን ፡ እንመልስለት ፡ ያልነው ፡ በነውር ፡ ከሚገመት ፡ ሀብት ፡ እንድንርቅ ፡ ነው ። የውለታ ፡ መንገድ ፡ መጥረጊያው ፡ ይህ ፡ ነው ።

# 484

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጤ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በመንበረ ፡ ጸባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ አዲስ ፡ የተሠራውን ፡ የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ሕንጻ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ.ም. በ፲ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲመርቁ ፡ የተናገሩት ፡ ቃሎች ።

ሀ) የማኅበሩ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የክቡር ፡ ሌ ኰሎኔል ፡ ተአምራት ፡ ይገዙ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ለሕዝብዎ ፡ ልማት ፤ ለወጣቶችዎ ፡ ምኞት ፤ ማሰብን ፡ የዕለት ፡ ተግባርዎ ፡ አድርገው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መስፋፋትና ፡ እድገት ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚደክሙ ፡ ግርማዊነትዎ ፤ በሌላው ፡ ዓለም ፡ ክፍል ፡ የሚ



ደረገው ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ወጣቶች ፡ ተገዥዎችዎ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ በማሰብ ፤ ከመቶ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ለወጣቶች ፡ አገልግሎቱን ፡ ሲሰጥ ፡ የኖረው ፡ የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ የተባለው ፡ ድርጅት ፤ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትግዛትዎ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቋቋም ፡ ፈቅደው ፡ ሥራው ፡ በፍጥነት ፡ እንዲጀመር ፡ አዘዙ ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ ከሕዝብ፡ በሚዋጣ ፡ ገንዘብ ፡ የሚካሄድ ፡ ድርጅት ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፤ ለመጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ በችሮታ ፡ የሰጡት ፡ ኻያ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አጀማመር ፡ መልካም ፡ ክንውን ፡ ሊያስገኝለት ፡ ችሏል ። እንዲሁም ፡ ለማኅበሩ ፡ የበላይ ፡ ጠባቂ ፡ ለመሆን ፡ መፍቀድዎ ፡ ለማኅበሩ ፡ ክብርና ፡ ሞገስ ፡ ሆኖታል ። ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ለማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ይሠራበት ፡ ዘንድ ፡ ለድርጅቱ ፡ በሚስማማ ፡ ስፍራ ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ካሬ ፡ ሜትር ፡ ቦታ ፡ ሰጥተው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ፲፱ነኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ.ም. የማኅበሩን ፡ ቤት ፡ የመጀመሪያ ፡ መሠረት ፡ ድንጋይ ፡ አስቀመጡልን ። በዚያም፡ ዕለት ፡ “ይህ ፡ ማኅበር ፡ ዓላማውን ፡ በሰፊ ፡ ምቾት ፡ ለማከናወን ፡ ይችል፡ ዘንድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወጣቶች ፡ በፍቅር ፡ አስተባብሮ ፡ ከሌላው ፡ ዓለም ፡ ወጣቶች ፡ በማስተዋወቅ ፡ ወደ ፡ ተሻለ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ለማድረስና ፡ በመንፈስ ፡ በአእምሮ ፤ በአካላዊ ፡ ጥንካሬ ፡ ለማደርጀት ፡ ለሚደከምበት ፡ ሥራ ፡ እርዳታችንና ፡ ሐሳባችን ፡ ከዚህ ፡ ድርጅት ፡ አይርቅም” ፡ ሲል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለማኅበሩ ፡ የሰጠው ፡ ንጉሣዊ ፡ ተስፋ ፤ ለማኅበሩ ፡ ሥራ፡ አስኪያጆች ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የሥራ ፡ ትጋትን ፡ አሳድሮባቸዋል ።

እንዲሁም ፡ ለማኅበሩ ፡ ቤት ፡ ማሠሪያ ፡ ከቸሩት ፡ አምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ለሥራው ፡ ፍጻሜ ፡ በየጊዜው ፡ በተደረገልን ፡ ድጋፍ ፡ ይኸው ፡ ቤቱ ፡ አልቆ ፡ ዛሬ ፡ ፍጻሜ ፡ ታየ ።

ጃንሆይ ።

ይህ ፡ ዛሬ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ አግኝቶ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የሚመረቀው ፡ ሕንፃ ፡ የፈጀው ፡ Eth. $205.838. ነው ። ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፡ Eth. $50.000 ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ሲሰጥ ፤ ጀኔቭ ፡ ከሚገኘው ፡ ከዓለም ፡ ወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡

ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ Eth. $24.800 እርዳታ ፡ አግኝተናል ። እንዲ
ሁም ፡ ከግብጽ ፡ ናሽናል ፡ ካውንስል ፡ Eth. $12.500 ደርሶናል ። ስለዚ
ህም ፡ የማኅበሩ ፡ ወንድሞች ፡ የሆኑ ፡ ድርጅቶች ፡ ላደረጉት ፡ እርዳታ ፡
ከግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ምስጋና ፡ ሳላደርግ ፡ አላልፍም ።
ከዚህ ፡ በተረፈው ፡ Eth. $128.538 Eth. $19.700 ብቻ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊ
ት ፡ የምንሰበስበው ፡ ሰዳ ፡ ሲኖርብን ፡ Eth. $108.838 የማኅበሩን ፡ ጠቃ
ሚነት ፡ ከሚያምኑ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚገኙ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝቦች ፡
የተሰበሰበ ፡ ነው ። ይህም ፡ የገንዘብ ፡ ሰብሰባ ፡ ክንውን ፡ ሥራውን ፡ ከጀመ
ርን ፡ ጀምሮ ፡ ማኅበሩ ፡ ባሳየው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ የተገኘ ፡ ውጤት ፡ ነው ፡
ለማለት ፡ ይቻላል ።

የአዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ የሐሳብ ፡ ደጋፊነት ፡ ይህን፡
ለትውልድ ፡ የሚያልፍ ፡ የጋራ ፡ ቤት ፡ ተባብሮ ፡ በመሥራቱ ፡ ሲደሰትበ
ትና ፡ ሲኰራበት ፡ ይኖራል ። እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ማኅበር ፡ መሪነት ፡ የአ
ንድ ፡ ከተማ ፡ ሕዝብ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ያለበትን ፡ ኀላፊነት ፡ በመገ
ንዘብ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ በኅብረት ፡ ለመሥራት ፡ እንደሚ
ችል ፡ የጋለ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ከዚህ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ተስፋ ፡
ወጣቶች ፡ ክፉንና ፡ በጎን ፡ በማወቅ ፤ በብርሃን ፡ ፋና ፡ እየተመሩ ፡ ለሀገራ
ቸው ፡ ታማኝና ፡ ዐዋቂ ፡ የትውልድ ፡ ራስ ፡ ለመሆን ፡ ለተቀደሰ ፡ ተግባር ፡
የሚዘጋጁበት ፡ እንዲሆን ፡ ነው ። ስለማኅበሩ ፡ አቋቋምና ፡ መሠረታዊ ፡
አሳብ ፡ ባጭሩ ፡ እናገራለሁ ። ይህ ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ፍላጎቱ ፡ የዓለምን ፡
ሕዝቦች ፡ ወገንና ፡ ባዕድ ፡ ሃይማኖትና ፡ ቀለም ፡ ሳይለይ ፡ ሁሉንም ፡ በአ
ንድ ፡ ላይ ፡ አስተባብሮ ፡ በማቀራረብ ፡ በመካከላቸው ፡ የወንድማማችነት፡
መንፈስ ፡ በመፍጠር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የግል ፡ ጉዳዩንና ፡ ጥቅሙን ፡ ብቻ ፡
ሳይመለከት ፤ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ሰላም ፡ የሚመች ፡ ሥራ ፡ የመሥራት ፡
መንፈስ ፡ እንዲያድርበትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ በምድር ፡
ላይ ፡ ለማሳወቅ ፡ ነው ። ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ በፍቅር ፡
በመተሳሰር ፡ በመካከላቸው ፡ በጎ ፡ ምግባርን ፡ በመሥራት ፡ ሌሎች ፡ ወገ
ኖቻቸውንም ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ለመምራት ፡ የሚያስቡትን ፡ መን
ፈስ ፡ በአእምሮዋቸው ፡ መቅረጽና ፡ ወጣቶች ፡ በእድገታቸው ፡ ሙሉ ፡
የማስተዋልን ፡ ችሎታና ፡ በዕውቀት ፡ የመስፋፋትን ፡ ዕድል ፡ እንዲያ
ገኙ ፡ መርዳት ፡ በማኅበራዊም ፡ ኑሮ ፡ ያለባቸውን ፡ ኀላፊነት ፡ ማሳወቅ ፡



የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ማኅበር ፡ አገልግሎቱን ፡ በሚፈጽምባቸው ፡ በ፸፰ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ፡
አንድ ፡ ዐይነት ፡ ዓላማ ፡ አለው ። ይኸውም ፡ ወጣቶችን ፡ በአእምሮ ፡
ብሩህ ፡ በመንፈስ ፡ ጽኑ ፡ በአካላዊ ፡ ጥንካሬ ፡ ሙሉ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡
ድርጁ ፡ አድርጎ ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ በመምራት ፡ ለአገራቸው ፡ ታማኝና ፡
መልካም ፡ ሕዝቦች ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ምንም ፡ በዓላማዊና ፡
በሥራው ፡ አመራር ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ቢሆንም ፡ ሥራው ፡ የሚካሄደ
ውና ፡ የሚጠበቀው ፡ በዚያው ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ በሚገኙ ፡ ሕዝቦች ፡ ነው።
ፕሮግራሙንም ፡ የሚያካሂደው ፡ ለሀገሩ ፡ በሚስማማ ፡ ዓይነት ፡ የሀገሩ ፡
ልማድና ፡ ባህል ፡ ሳይደመሰስ ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁናቴ ፡ እያየ ፡ ነው ።
ሥራው ፡ የሚካሄደው ፡ በዚያው ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ እንደመሆኑም ፡
መጠን ፡ ለሥራው ፡ ማስኬጃ ፡ የሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኘውና ፡ የሚ
ደግፈው ፡ ከዚያው ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙ ፡ ሕዝቦች ፡ ነው ። ይህም ፡
በማኅበርተኝነት ፡ ከሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በቀር ፤ ወጣቶች ፡ በዕውቀት ፡
የጐለመሱ ፡ መልካምና ፡ ታማኝ ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲሆኑ ፡ ለመርዳት ፡ ቅን ፡
መንፈስና ፡ ፍላጎት ፡ ካላቸው ፡ አስተዋይ ፡ ሰዎች ፡ ከሚሰጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ችሮታ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ለሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ ከወሰን
ነው ፡ ባጀት ፡ Eth. $35.843 ውስጥ ፡ ኒውዮርክ ፡ የሚገኘው ፡ የእንቴርና
ሲዮናል ኮሚቴ ፡ Eth. $21.638 ርዳታ ፡ ሲሰጠን ፤ የቀረው ፡ Eth. $
14.205 ፡ የሞላው ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙ ሕዝቦቹ ፡ በማኅበረተኛነ
ትና ፡ በስጦታ ፡ ካገኘነው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። ለአሁኑ ፡ ለያዝነው ፡ ዓመተ ፡ ዳ
ግም ፡ Eth. $48.495 ባጀት ፡ ተወስኗል ። ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ የኢንቴርና
ሽናል ፡ ኮሚቴ ፡ Eth. $19.991 ፡ የሚረዳን ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጠናል ።
ከዚህም ፡ የቀረውን ፡ Eth. $28.504 ግን ፡ ከሀገር ፡ ውስጥ ፡ ማግኘት ፡
ስላለብን ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝቦች ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ላደረጉት
ችሮታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናችንን ፡ እያቀረብን ፤ እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ዓ
መት ፡ ለዚህ ፡ ለማይቋረጥ ፡ አገልግሎታችን ፡ የተለመደ ፡ ልግስናቸውን ፡
እንዳይነሱን ፡ እንጠይቃለን ። በኒውዮርክ ፡ የሚገኘው ፡ የኢንተርናሲዮ
ናል ፡ ኮሚቴ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ እርዳታ ፡ በያመቱ ፡ ከማድረጉ ፡ በላይ ፤ የዚ

ህን ፡ ማኅበር ፡ ሥራና ፡ እንዲሁም ፡ ወጣቶቹን ፡ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ የማሠልጠን ፡ ልምድ ፡ ያላቸውን ሚስተር ፡ መርለን ፡ አ ፡ ቢሾፕ ፡ የተባሉ ፡ አሜሪካዊ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ሙሉ ፡ ደሞዛቸውን ፡ እየከፈለ ፡ የሚያሠራልን ፡ በመሆኑ ፡ ደግሜ ፡ አመሰግናለሁ ።

ሚስተር ፡ መርለን ፡ አ ፡ ቢሾፕ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተላኩበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በዋናው ፡ ጸሐፊነት ፡ ሲያገለግሉ ፡ ለማኅበሩ ፡ ያስገኙት ፡ ሰፊ ፡ እርምጃና ፡ ቅን ፡ አገልግሎት ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ከሚያስመሰግናቸው ፡ ችሎታ ፡ ጋር ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ጠባይ ፡ የተመሉ ፤ እምነት ፡ ሊጣልባቸው ፡ የሚችሉ ፡ ሰው ፡ በመሆናቸው ፡ ስላደረጉት ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ አመሰግናቸዋለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ ሞያ ፡ እናውለው ፡ ዘንድ ፡ ለመልካም ፡ ሥራ ፡ ከፍቶ ፡ ሲመርቅልን ፤ በዚህ ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከነበርንበት ፡ ሥፍራ ፡ የበለጠ ፡ አገልግሎት ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስችለን ፡ መሆኑን ፤ በሚገባ ፡ እየተረዳን ፤ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ እንሰጥ፡ ከነበረው ፡ ፕሮግራም ፡ በበለጠ ፡ ሁናቴ ፡ እያዘጋጀን ፡ ለወጣቶች ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ አገልግሎት ፡ እናካሂድበታለን ።

በዚህም ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዳችን ፡ በኀላፊነት ፡ ልንፈጽመው ፡ የሚገባን ፡ ተግባር ፡ ይኖርብናል ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያው፡ ዓመት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ከግርማዊነትዎም፡ እርዳታ ፡ ጋር ፡ የሥራ ፡ ዕቅዳችን ፡ ሁሉ ፡ ከፍጻሜ ፡ እንደሚደርስልን ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ይህን ፡ በአገራችን ፡ አዲስ ፡ የተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ በማካሄድ ፡ ከዚህ ፡ ደረጃ ፡ ለማድረስ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ የመሪነት ፡ ተግባራቸውን ፡ ለፈጸሙ ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፤ ለዲሬክተሮቹ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ፤ የጀግኖች ፡ ማኅበር ፡ ቤቱን ፡ አውሶን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ስንገለገልበት ፡ እንድንቈይ ፡ ስላደረገልን ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ። ይህን ፡ ቤት ፡ ለማሠሪያ ፡ የሚሆን፡



ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ሲደከምበት ፡ ለነበረው ፡ ሥራ ፡ የቅርብ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ደንበኛውን ፡ አገልግሎት ፡ ለፈጸሙልን ፡ ለክቡር ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማና ፡ ለክቡር ፡ አቶ ፡ ምናሴ ፡ ለማ ፡ እንዲሁም ፡ ለአቶ ፡ አብደላ ፡ ሳሊም ፡ በዓጊል ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የማኅበሩ ፡ ጸሐፊ ፡ የምስተር ፡ መርለን ፡ ቢሾፕ ፡ ንግግር ፤

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህ ፡ አዲስ ፡ የወ. ወ. ክ. ማ. ሕንፃ ፡ መከፈት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምረን ፡ በናፍቆት ፡ እንጠብቀው ፡ የነበረ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ቤት ፡ ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሲመርቁልንና ፡ በሩን ፡ ከፍተው ፡ ሲሰጡን ፡ ክብር ፡ አስገኝተውልናል ። በዚህም ፡ ትልቅ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ የአመራርዎን ፡ ሥርዓት ፡ አድንቀናል ። ለዜጎችዎም ፡ መልካም ፡ መስፋፋት ፡ በአደረጉት ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ተደስተናል ።

ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆኑት ፡ ለዕውቀትና ፡ ለሰብአዊ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ዝንባሌዎ ፡ የሚያመዝን ፡ በመሆን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየትዎን ፡ እጅግ ፡ አድንቄያለሁ ። በአስተዋይነትዎም ፡ ከሚያቅዱዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ውጤቱን ፡ እናያለን ። ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ወ . ወ . ክ . ማ . ለኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ሥራውን ፡ እንዲያካሂድ፡ ጠየቁ ። እኔም ፡ ለወጣቶች ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ፕሮግራም ፡ እያካሄድኩ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እንዳገለግል ፡ በመመረጤ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶኛል ።

ይህን ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. በአበባ ፡ ለማስጌጥ ፡ አስቀድሞ ፡ ማረስና ፡ መትከል ፡ ያሻል ። በጥበባዊ ፡ አስተያየትዎ ፡ ሥራው ፡ እንዲጀመር ፡ በመጠበቅ ፡ ዘሩን ፡ ተክለዋል ። በምርቃትዎም ፡ ወጣቱን ፡ አትክልት ፡ ውሃ ፡ አጠጥተውታል ፤ ለማኅበሩ ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ቦታ ፡ ሰጡ ፤ የቤቱን ፡

መሠረት ፡ ማዕዘን ፡ ድንጋይ ፡ አስቀመጡ ። በገንዘቡም ፡ ስጦታ ፡ ያደረጉት ፡ ልግስና ፡ ሌሎች ፡ እንዲከተሉ ፡ መልካም ፡ ምሳሌነትን ፡ ፈጠረ ፤ ለማድረግ ፡ ለሞከርነው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምርቃትዎን ፡ አበረከቱልን ። በዚህ ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ድንጋዮች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በጥንቃቄ፡ የተገነቡ ፡ ናቸው ። ሺው ፡ ድንጋዮች ፡ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ የመጡትንና ፡ ሌሎችንም ፡ ወደፊት ፡ የሚመጡ ፡ ሺህ ፡ ወጣቶች ፡ ያመለክታል ።

ወ. ወ. ክ. ማ. በዓለም ፡ ዙሪያ ፡ የታወቀና ፡ በ፸፰ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ በሚሊዮን ፡ ለሚቈጠሩ ፡ ወጣቶች ፡ አገልግሎቱን ፡ የሚሰጥ ፡ ቢሆንም ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ቆራጭ ፡ የሆነ ፡ የበላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የለውም ። በያንዳንዱ ፡ አገር ፡ የሚጠበቀውና ፡ የሚካሄደው ፡ በሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ጉባኤ ፡ ሆኖ ፡ የሚደገፈውም ፡ ወጣቶች ፡ በተድላ ፡ እንዲያድጉና ፡ ለሀገራቸው ፡ ታማኝ ፡ ሕዝቦች ፡ እንዲሆኑ ፡ ዕድልን ፡ ለመስጠት ፡ ከሚሹ ፡ ሰዎች ፡ በሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፤ ስለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ በታማኝነት ፡ ለአደረጉት ፡ ድገፉ ፡ በተለይ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነውን ፡ የደስታ ፡ ስሜቴን ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ስገልጽ ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኔ ፡ ይሰማኛል ፤ በክቡር፡ ኰሎኔል ፡ ታምራት ፡ ይገዙ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ መሪነት ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ ተራምዷል ። ይህም ፡ ዛሬ ፡ የሚመርቁት ፡ ሕንፃ ፡ ለቤቱ ፡ ማሠሪያ ፡ ለሚሰበሰበው ፡ ገንዘብ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሆነው ፡ ከልብ፡ የሆነ ፡ የሥራ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ከሰጡት ፡ ከክቡር ፡ ኰሎኔል ፡ ክፍሌ፡ ዕርገቱ ፡ የተገኘ ፡ የሥራ ፡ ውጤት ፡ ነው ። በሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ትጋትና ፡ አመራር ፡ በሺህ ፡ በሚቈጠሩ ፡ ወዳጆቻችን ፡ እርዳታ፡ በወጣቶቻችን ፡ መካከል ፡ መልካም ፡ ጠባይንና ፡ ታማኝ ፡ ሕዝብነትን ፡ ለመመሥረት ፡ የሚያስችለው ፡ ይህ ፡ መታሰቢያቸው ፡ የሚሆን ፡ ሕንፃ ፡ ለፍጻሜ ፡ በቃ ። ለምለም ፡ መሬት ፡ የመልካም ፡ መከር ፡ እርሻ ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችል ፡ ያህል ፡ ጥሩ ፡ ቤት ፡ ጥሩ ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. አያደርግም ፡ በወ. ወ. ክ. ማ. ማሳ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ዘሮች ፡ በክበባችን ፡ አባል ፡ የሆኑና ፡ በሰው



ነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ሥራችን ፤ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ ክፍላችን ፤ በቲያትርና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፕሮግራማችን ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ የሚገኙ ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩት ፡ ወጣቶች ፡ ናቸው ። እንዳስተዋልኩትም ፡ በሌላም ፡ ዓለም ፡ ከሚገኙ ፡ ወጣቶች ፡ ጋር ፡ በችሎታ ፡ እኩልነት ፡ ያላቸውና ፡ ባለብሩህ ፡ አእምሮ ፡ ታማኝ ፡ ወጣቶች ፡ መሆናቸውን ፤ ተመልክቻለሁ ። በዚህም ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ አለኝ ። ክበቦቻችንንና ፡ የስፖርት ፡ ክፍላችንን ፡ እንዲሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ፕሮግራማችንን ፡ ለተማሩ ፡ ወጣቶቻችን ፡ ማስፋፋትና ፡ ማካሄድ ፡ ብቻ ፡ ትምህርትን ፡ ለማግኘት ፡ ዕድል ፡ ሳይኖራቸው ፡ የቀሩትን ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎችን ፡ ፍላጎት ፡ ለመሙላት ፡ ያለብንን ፡ ኀላፊነት ፡ አይቀንስልንም ።

እነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ለመርዳት ፡ ወ . ወ . ክ . ማ . የትምህርት ፡ ክፍልና፡ ንግግሮች ፤ እንዲሁም ፡ የመወያያ ፡ ጊዜ ፡ እያዘጋጀ ፡ የዕለት ፡ ኑሮን ፡ መሠረታዊ ፡ መክፈቻ ፡ ለመስጠት ፡ አማርኛ ፡ ጽሕፈትና ፡ ንባብ ፤ ጤና ፡ አጠባበቅንና ፡ አመጋገብን ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ሁሉ ፡ በማስተማር ፡ ለመርዳት ፡ ይሞክራል ። በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ያለብንን ፡ ኀላፊነት ፡ የተሟላ ፡ ለማድረግ ፡ የምንችለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ የሆነውን ፡ የሕይወት ፡ መንገድ ፡ የሚገኝበትን ፡ እርዳታ ፡ ለመስጠት ፡ ራሳችንን ፡ አሳልፈን ፡በመስጠት ፡ ነው ። ወጣቶቻችንን ፡ ልንረዳ ፡ የሚገባንን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አልፈጸምንም ። ይህ ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ በውነቱ ፡ ሊረዳን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወደፊት ፡ የሥራ ፡ ዕቅዳችን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ድርጅት ፡ ይጨምራል ።

በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ ለሆኑት ፡ ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ የተደላደለ ፡ ችሎታ ፡ ስናገኝ ፡ በሥራችን ፡ ተመክተን ፡ አንደሰትም ። በሚሰጠው ፡ ትምህርትና ፡ አመራር ፡ የሕይወት ፡ ኑሮዋቸው ፡ የተሟላ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በቤታቸውም ፡ ተደሳች ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይሆናሉ ። የአዲስ ፡ አበባ ፡ ወ. ወ. ክ. ማ. እርሻ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጥ ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ማጠጣትና ፡ ማዳበር ፡ ያሻዋል ። አትክልተኛ ፡ ለሆኑት ፡ አብረውኝ ፡ ለሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብ ፡ ይገባኛል ፡ በቅን ፡ አገልግሎታቸው ፡ ውሃ ፡ አጠጥተዋል ፡ አዳብረውማል ። ወጣቶቹ ፡ ተክሎች ፡ አምረዋል ። ለመልካም ፡ መከር ፡ የሚታደሉ ፡ መሆናቸውም ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። የወ. ወ. ክ. ማ. እርሻ ፡ ብዙ ፡ ምርት ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ፡ የሠሩ ፡ ብዙዎች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ጊዜያቸውን ፡

ሰጥተው ፡ ባይረዱን ፡ ኖሮ ፤ ወጣቶቹን ፡ ተክሎች ፡ ለማሳደግ ፡ ባልቻልንም ፡ ነበር ። በዚህ ፡ አዲስ ፡ ቤታችን ፡ ተጨማሪ ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ለመርዳት ፡ እንችላለን ። ዓላማችን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ እንዲያድግ ፡ ለመርዳት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በመንፈስ ፡ በአካላዊ ፡ ጥንካሬ ፡ በአእምሮ ፡ እንዲደረጅ ፡ መርዳት ፡ ያሻናል ። ዓላማችን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪውን ፡ መስሎ ፡ እንዲያድግ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ በእውነት ፡ ጠንካራ ፡ በአካባቢው ፡ ከሚገኘው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እንዲወጣው ፡ ነው ። የዚህም ፡ የመጨረሻው ፡ ውጤት ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያለው ፡ ጠባየ ፡ መልካምና ፡ ፈጣሪውን ፡ ወዳጅ ፡ ለሀገሩ ፡ ታማኝ ፡ ለሌሎች ፡ መልካም ፡ ለማድረግ ፡ አዘውትሮ ፡ የመውደድ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ነው ።

የወ. ወ. ክ. ማ. ሥራ ፡ ክንውን ፡ የሚገመተው ፡ በየጊዜው ፡ በሚያስገኘው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ነው ። ግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ የዚህን ፡ ትልቅ ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ለታማኝነትና፡ ለመልካም ፡ ፍሬ ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ሆኖ ፡ እንዲያገኙት ፡ የዘወትር ፡ ጸሎታችን ፡ ነው ።

* * *

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ ለዓለም ፡ ወጣቶች ፡ አእምሮአቸውን ፡ በማጐልመስ ፡ ባሕሪያቸውን ፡ በማረም ፡ መንፈሳቸውን ፡ በማነቃቃት ፡ ባገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቋቁሞ ፡ ለማየት ፡ የነበረን ፡ ምኞት ፡ ተፈጽሞ ፡ ሕዝባችን ፡ ይህንን ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ በሚያከብርበት ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ይኸንን ፡ አዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ስንከፍት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ። ይኸም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በመከፈቱ ፡ ትምህርት ፡ የአእምሮና ፡ የአካል ፡ እድገት ፡ የሚገኝባቸው ፡ ፕሮግራሞች ፡ በወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ አማካይነት ፡ እርግጠኛና ፡ ቀዋሚ ፡ በሆኑ ፡ መሠረቶች ፡ ላይ ፡ እንዲመሠረቱ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የተደረገው ፡ ድካምና ፡ መሥዋዕትነት ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳገኘ ፡ ሊቈጠር ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ ማኅበር ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ባለማሰብ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በውጭ፡



አገር ፡ በሥራም ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ ከብዙዎቹ ፡ እርዳታን ፡ በማግኘት ፡ የተቋቋመ ፡ ስለሆነ ፡ ለሕዝባችንና ፡ ለሌሎች ፡ ክርስቲያናውያን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ የመንፈስ ፡ መበረታቻ ፡ ሆኖ ፡ ማገልገል ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ወጣቶቻችን ፡ ክርስቲያናዊ ፡ በሆነ ፡ አሳብና ፡ ኀይል ፡ እየተመሩ ፡ እንዲያድጉ ፡ ላለን ፡ እምነት ፡ እውነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ይህ፡ ሕንፃ ፡ በመንበረ ፡ ጸባዖት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴራችንና ፤ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ በመሆኑ ፡ የሚገባውን ፡ ሥፍራ ፡ ይዟል ። ስለዚህ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ተግባሮች ፡ ላካባቢዎቹ ፡ ቦታዎች ፡ ተገቢ ፡ ሆነው ፡ እንዲገኙ ፡ እንመኝለታለን ።

ይህ ፡ ማኅበር ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በመሆን ፡ በክርስቶስ ፡ ወንድማማችነትን ፡ ላገኘበት ፡ ከፍተኛ ፡ ሐሳብ ፡ ነዋሪ ፡ ምስክር ፡ ነው ። እንደ ፡ አውሮፓውያን ፡ አቈጣጠር ፡ ፲፰፻፶፭ ፡ ዓ.ም. የኢንተርናሲዮናል ፡ ወጣት ፡ ወንዶች ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ የመጀመሪያውን ፡ ስብሰባ ፡ ካደረገበት ፡ ጀምሮ ፡ ባለው ፡ በመቶ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ድርጅት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ ሰማኒያ ፡ በሚጠጉ ፡ አገሮች ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ አገልግሎት ፡ መፈጸሙን ፡ ማስታወስ ፡ የተገባ ፡ ነው ። የቦርዱ ፡ አባሎችና ፡ ሰክሬታሪው ፡ ሚስተር ፡ ቢሾፕ ፡ ሥራውን ፡ በመምራትና ፡ ሕንፃውን ፡ በማሠራት ፡ ባደረጉት ፡ አገልግሎት ፡ ደስ ፡ እንዳለን ፡ እንገልጣለን ። እግዚአብሔር ፡ ማኅበሩን ፡ እንዲረዳውና ፡ ሠራተኞቹን ፡ እንዲያከናውን ፡ እንመኛለን ።

# 485

የኦስትሪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር፡ ክቡር ፡ ኮንት ፡ አሊቬዩ ፡ ሬዚጊዩ ፡ ግንቦት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የነምሳ ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ እንድሆን ፡ ወደ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የተሾምኩበትን ፡

ደብዳቤ ፡ ለማቅረብ ፡ ሲፈቀድልኝ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የነምሳን ፡ ሕዝብና ፡ የመንግሥቴንም ፡ ምኞት ፡ ለመግለጽ ፡ ምክንያት ፡ በማግኘቴ ፡ ለእኔ ፡ ክብሬ ፡ ነው ።

ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትውልድ ፡ ጀምሮ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በነምሳ ፡ መካከል ፡ የተሳሰረ ፡ የቀድሞ ፡ ወዳጅነት ፡ አለ ። የዚህም ፡ የወዳጅነት ፡ ምልክት ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መልካም ፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ ነምሳን ፡ በጐበኟት ፡ ጊዜ ፡ የተከናነበችው ፡ ክብር ፡ በአገሬ ፡ ተወላጆች ፡ ልብ ፡ የማይረሳ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ። ግርማዊነትዎ ፡ ነምሳን ፡ ለመጐብኘት ፡ ምክንያት፡ ባገኙበት ፡ ጊዜ ፡ የነምሳ ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥቴ ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በሕዝብዎ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ግምት ፡ እንደነበረው ፡ ለማየት ፡ በመቻልዎ ፡ የምመሰገንበት ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖሩትና ፡ ለሚሠሩት ፡ ለነምሳ ፡ ተወላጆች ፡ ሁሉ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ለተደረገላቸው ፡ የመልካም ፡ አድራጎት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ለማመስገን ፡ ይፈቀድልኝ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የልብ ፡ ታዛዥነትና ፡ የጥልቅ ፡ ወሮታ ፡ መላሽ ፡ መሆናቸውን ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ በእነሱ ፡ ስም ፡ ለመግለጽ ፡ መርሳትን ፡ አልፈቅድም ።

ንግግሬንም ፡ በመፈጸም ፡ በነምሳ ፡ ሕዝብና ፡ በመንግሥቴ ፡ ስም ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ አኗኗር ፡ የማቀርበውን ፡ መልእክት ፡ መልካም፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ ልመናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የኦስትሪያ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ በመሾምዎ ፡ ከክቡር ፡ የኦስትሪያ ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዴንት ፡ የተሰጠውን፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ በደስታ ፡ ነው ። በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የቈየውን ፡ ጽኑ ፡ የወዳጅነት ፡ መተሳሰሪያ ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ ገልጠውታል ። በተዋበች ፡ አገርዎ ፡ ያሳ



ለፍናቸው ፡ ቀኖች ፡ ምንም ፡ አጭር ፡ ቢሆኑ ፡ የኦስትሪያ ፡ ሕዝብ ፡ ለእኛና ፡ ለሕዝባችን ፡ ያለውን ፡ የወዳጅነት ፡ መልካም ፡ ስሜት ፡ ራሳችን ፡ ልንገነዘብባቸው ፡ ችለናል ። ኦስትሪያ ፡ ነፃነቷን ፡ እንድታገኝ ፡ የተመኘነውና ፡ የገለጽነው ፡ ጥልቅ ፡ ምኞት ፡ ተፈጽሞ ፡ በመስማታችን ፤ የኦስትሪያ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ደስታ ፡ ተካፋዮች ፡ መሆናችንን ፡ ለመንግትዎ ፡ ቢገልጹልን ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ክቡርነትዎን ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ በደስታ ፡ ስንቀበልዎ ፡ በኦስትሪያና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ እውነተኛ ፡ ወዳጅነት ፡ የበለጠ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማደርጀት ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ በጎ ፡ አስተያየት ፡ የሚኒስትሮቻችንና ፡ የሕዝባችን ፡ እርዳታ ፡ የማይጓደልብዎ ፡ መሆኑን ፡ ልናረጋግጥልዎ ፡ እንወዳለን ። በመንግሥትዎና ፡ በኦስትሪያ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ስለገለጡልን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እያመሰገንን ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ለክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱና ፡ ለኦስትሪያ ፡ ሕዝብ ፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት፡ ከሰላምታችን ፡ ጋር ፡ እንዲያቀርቡልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 486

የፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ ጃክ ፡ ባያን ፡ ግንቦት ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ እንድሆን ፡ የተሾምኩበትንና ፡ እንዲሁም ፡ ከእኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሙሴ ፡ ሔንሪ ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊነ

ትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

የግርማዊነትዎ ፡ የ፳፫ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ዓመት ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ እንዳከናውን ፡ የተሰጠኝ ፡ ሥራ ፡ ለእኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ሕሊናዬን ፡ የሚቀሰቅሰው ፡ ይሆናል ።

ዘግርማዊነትዎ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ብርሃናዊ ፡ መሪነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛትዎ ፡ ውስጥ ፡ የተከናወኑትን ፡ ግሩም ፡ የሆኑ ፡ እርምጃዎች ፡ ለማየት ፡ መላው ፡ ፈረንሣይ ፡ ከዚህ ፡ በዓል ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ከጥቂት ፡ ወራቶች ፡ በፊት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በፓሪስ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሣይ ፡ ሕዝብ ፡ ያደረገልዎ ፡ አቀባበል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ በፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የፍቅር ፡ ግንኙነት ፡ በበለጠ ፡ ሳያደረጀው ፡ አልቀረም ።

ካለፉት ፡ ብዙ ፡ ዓመታቶች ፡ ጀምሮ ፡ የተገለጸውን ፡ ወዳጅነትና ፡ እንዲሁም ፡ ኢትዮጵያና ፡ ፈረንሣይን ፡ በታሪክ ፡ ያስተሳሰራቸውን ፡ አንድነት ፡ በበለጠ ፡ ለማስፋፋት ፡ በተቻለኝ ፡ ሁሉ ፡ የምደክም ፡ መሆኔን ፡ በበኩሌ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ላረጋግጥልዎ ፡ እወዳለሁ ።

የፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ኰቲ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ፈረንሣይ ፡ አገር ፡ በተቀበሉት ፡ ጊዜ ፡ ተሰምቷቸው ፡ የነበረውን ፡ ደስታ ፡ እንድገልጽልዎ ፡ ታዝዣለሁ ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ የፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ጸጋ ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለሕዝብዎ ፡ ልማት ፡ ያላቸውን ፡ ምኞት ፡ እንድገልጽ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የታዘዝኩትን ፡ መልእክት ፡ ሳቀርብ ፡ ደስ ፡ እያለኝ ፡ ነው ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የፈረንሣዊ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ በመሾምዎ ፡



ከክቡር ፡ የፈረንሣዊ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተሰጠዎትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡
ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ በደስታ ፡ ነው ።

ከርስዎ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የተከበሩ ፡ አምባሳደር ፡ የተጠሩበትን ፡
ደብዳቤ ፡ በምንቀበልበት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ሔንሪ ፡ በፈረንሣዊና ፡
በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መግባባ
ትና ፡ መተባበር ፡ በበለጠ ፡ ለማጽናትና ፡ ለማስፋፋት ፡ ያደረጉትን ፡ መል
ካም ፡ አገልግሎት ፡ ሳናስታውስ ፡ አናልፍም ።

የፈረንሣዊን ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ በጐበኘንበት ፡ ባለፈው ፡ ቅርብ ፡
ጊዜ ፡ የፈረንሣዊ ፡ ሕዝብ ፡ ለኛና ፡ ለሕዝባችን ፡ ያለውን ፡ ፍቅርና ፡ የወዳ
ጅነት ፡ ስሜት ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ አይተን ፡ ለመረዳት ፡ ችለናል ። ይህ ፡
በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የወዳጅነትና ፡ የመግባባት ፡ መን
ፈስ ፡ ባለፈው ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ግንኙነታቸውን ፡ እንዳጸናው ፡ ሁሉ ፡
በሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ በመካከላቸው ፡ የሚኖረውን ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙ
ነት ፡ እያስፋፋና ፡ እያደረጀ ፡ እንደሚሄድ ፡ ያለንን ፡ ምኞት ፡ ስንገልጽ
ደስ ፡ ይለናል ። ክቡርነትዎ ፡ በፈረንሣዊና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መን
ሥት ፡ ግዛታችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጥንታዊ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት
ለማጠንከር ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ በጎ ፡ አስተያየት
የመንግሥታችንና ፡ የሕዝባችን ፡ እርዳታ ፡ እንደማይጓደልብዎ ፡ እናረጋ
ጥልዎታለን ።

ለክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ረኔ ፡ ኮቲ ፡ የወዳጅነት ፡ ሰላምታችንንና
እንደዚሁም ፡ ለፈረንሣዊ ፡ ሕዝብ ፡ ደስታና ፡ ብልጽግና ፡ ያለንን ፡ መል
ካም ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 487

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በአባ ፡ ዲና ፡ የፖሊስ ፡ ከፍተ
መኰንኖች ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በአራተኛው ፡ ኮርስ ፡ ለሠለጠኑት ፡ ፷፪ ፡ እጩ
መኰንኖች ፡ ግንቦት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ዲፕሎም ፡ ሲሰጡ ፡
ናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ከዚህ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታችሁ ፡ ተቃንቶላችሁ ፡ ስ
ወጡ ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ ለወጡት ፡ እጩ ፡ መኰንኖች ፡ የምስክር ፡ ወረ